# ለእምብርት የለሹ ምሁር

## ከጌትነት(ኖርዌ)

የአህያ በሬ
የጅብ “ገበሬ”
የዝንጀሮ ጎልጓይ
የጠጣ ዘር አቀባይ
ሁሉ እንብላው ባይ
በጅብ ቀዳ የተሠራ ክራር
ምን ቢቃኝ ምን ቢወጠር
መች ሞዝቆ ከእንብላው በቀር
ይውጣል
ይስለቅጣል
ያቦካል
ይፈተፍታል
ሆዳም ለዓመሉ መች ጠግቦ ያውቃል
የአፋን ሳይውጥ ሌላ ይመኛል
ስፌ ቀፈቱን ይዘረጥጣል
የወገን ስቃይ መች ታይቶት ያውቃል
አሮጌ ጅቡም እንዲያው ከቶ
በሶስት ስርዓት ሚስቶ
እየበላ አንኩቶ
የውሸት ባንዲራውን ለብሶ
ያሾፉል በሕዝብ ለቅሶ

ጎንባሳ ሆዳም